ጠቅላይ ሚኒስትሩ በህንድ የሀሳቦች ጉባኤ 2012 ላይ ያደረጉት ንግግር

ሐምሌ 15/2012 ዓ.ም

ሰላም፣

የንግድ መሪዎች፣

ክብራን እንግዶች፣

የዩኤስ- ህንድ ቢዝነስ ካውንስል በዚህ ‹የህንድ ሀሳቦች ጉባኤ› ላይ ንግግር እንዳደርግ ስለጋበዘኝ አመሰግናለሁ። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ አመት 45ኛ አመቱን የሚያከብረውን ዩኤስአይቢሲን እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እፈልጋለሁ። ባለፉት አስርት አመታት ዩኤስአይቢሲ የህንድን እና አሜሪካ ንግድ አቀራርቧል። የዩኤስአይቢ የዚህ አመት የሀሳብ ጉባኤ ምርጫ- ‹የተሸለ ነገን መገንባት› እጅግ በጣም ተገቢ ነው።

**ክቡራን ወዳጆች**

ሁላችንም እንደምንስማማበተ አለማችን የተሸለ ነገን ትፈልጋለች። ከዚህ በተጨማሪ ሁላችንም በጋራ የወደፊቱን ለመቅረጽ መሰራት አለበት። በጥብቅ እንደማምነው ለወደፊቱ ያለን አቀራረብ በዋናነት በሰው ላይ ትኩረት ያደረገ ሊሆን ይገባዋል። የእድገት አጀንዳችን ድሆችን እና ተጋላጮችን በዋናነት ማስቀደም አለበት። ‹ሕይወትን ማቅለል› እንደ ‹ንግድን ማቅለል› ጠቃሚ ነው።

**ክቡራን ወዳጆች**

የቅርቡ ጊዜ ልምድ እንዳስተማረን አለም አቀፍ ኢኮኖሚን በተወዳዳሪነት እና ትርፍን በማሳደግ ላይ ትልቅ ትኩረት ተደርጎ መቀየቱን ነው። ተወደዳሪነት ጥሩ ነው። ነገር ግን በሌላው ተመሳሳይ ጠቃሚ ነገር ላይ ትኩረት ማድረግ ከረሳን የውጭ ስጋቶች መቋቋም አለመቻላችንን ያመለክታል። ይህም አለም አቀፍ ወረርሽኝ አይበገሬነት ጠቃሚ መሆኑን ያስታውሰናል።

**ክቡራን ወዳጆች**

ህንድ የበለገጸ እና አይበገሬ አለም በ‹አትማኒባር ባራት›ጥሪ መሰረት ለማሳካት አስተዋጽኦ እያደረገች ነው። ለዚህም የእናንተን አጋርነት እንጠብቃለን።

**ክቡራን ወዳጆች**

ዛሬ በህንድ አለም አቀፍ አዎንታዊነት አለ። ይህ የሚሆነው ህንድ የተቀናጀ ትክክለኛ ግልጽት፣ እድል እና አማራጭን በማቅረቧ ነው። ይህንን ላብራራ። ህንድ በሰዎች እና በመንግስት መካከል ግልጽነት ያለበት አሰራር ዘርግታለች። ክፍት ገበያ ወደላቀ ብልጸግና ይመራል። እነዚህ መርሆዎች በህንድ እና በዩኤስኤ ስምምነት ላይ ተደርሶባቸዋል።

**ክቡራን ወዳጆች**

ባለፉት 6 አመታት ኢኮኖሚያችን የበለጠ ክፍት እንዲሆን እና ለውጥ ተኮር እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ስናደርግ ቆይተናል። ለውጦች ተወዳዳሪነትን በመጨመር ግልጸኝነትን በማስፈን ዲጂታይዜሽን በማስፋፋት የበለጠ ፈጠራ እና የፖሊሲ ዘላቂነትን ያረጋግጣል።

**ክቡራን ወዳጆች**

ህንድ የእድሎች አገር ሆናለች። ህንድ በአርሶ አደሮቻችን ጠንካራ ስራ ላይ ኢንቨስት እንድታደርጉ ትጋብዛለች። ህንድ በቅርቡ በእርሻ ዘርፍ ላይ ታሪካዊ ለውጥ አድርጋለች። የኢንቨስትመንት አማራጮች፡ በእርሻ ግብአቶች እና ማሽነሪ፣ የእርሻ አቅርቦት ትስስር አስተዳደር፣ የተዘጋጀ እቃዎች፣ የአሳ ምርት እና ኦርጋኒክ ምርቶች ላይ የኢንቨስትመንት እድሎች አሉ። የህንድ የምግብ ማቀነባበሪያ ዘርፍ እ.ኤ.አ በ2025 ከግማሽ ትሪሊየን ዶላር በላይ እንደሚሆን ይገመታል። የበለጠ የገቢ ምንጭ ለማሳደግ በህንድ በእርሻ ዘርፍ ኢንቨስትመንት ተጠቃሚ ለመሆን ጊዜው አሁን ነው።

ህንድ በጤናው ዘርፍ ኢንቨስት እንድታደርጉ ትጋብዛለች። በህንድ የጤናው ዘርፍ በአመት ከ22% በላይ እያደገ ይገኛል። ኩባንያዎቻችን በሜዲካል-ቴክኖሎጂ ምርት፣ ቴሌሜዲሲን እና ምርመራ እድገት እያሳዩ ይገኛሉ። ህንድ እና ዩናይትድስቴትስ በፋርማሲ ዘርፍ አጋርነታቸውን እያጎለበቱ ይገኛሉ። ደረጃውን በፍጥነት ለማሳደግ ጊዜው በህንድ በጤና ጥበቃ ዘርፍ ላይ ኢንቨስትመንቶን የሚያሰፉት ትክክለኛ ጊዜ አሁን ነው።

ህንድ በሐይል ዘርፍ ኢንቨስት እንድታደርጉ ትጋብዛለች። ህንድ በጋዝ ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ያላት በመሆኑ በዩኤስ ኩባንያዎች ትልቅ ኢንቨስትመንት እድል ይኖራል። ከዚህ በተጨማሪ በሀይል ዘርፍ ትልቅ እድል አለ። ለኢንቨስትመንቱ የበለጠ ሀይል ለማስገኘት በህንድ የሀይል ዘርፍ ላይ ለመሳተፍ ትክክለኛ ጊዜ አሁን ነው።

ህንድ በመሰረተ ልማት ዘርፍ እንድትሳተፉ ትጋብዛለች። ሀገራችን በታሪካችን ውስጥ ትልቁን የመሰረተ ልማት ፈጠራ በማካሄድ ላይ ትገኛለች። ኑ እና ለሚኒየኖች ቤቶችን በአጋርነት እንገንባ ወይም ለሀገራችን መንገዶችን፣ አውራ ጎዳናዎችን እና ወደቦችን እንገንባ።

ሲቪል አቬሽን ሌላው ትልቅ የእድገት አቅም ነው። የአውሮፕላን መንገደኞች በሚቀጥሉት 8 አመታት ከእጥፍ በላይ እንደሚያድጉ ይጠበቃል። ከፍተኛ የህንድ የግል አየር መንገዶች በሚመጣው 10 አመት ጊዜ ውስጥ ከ1000 በላይ አውሮፕላኖችን ለማካተት አቅደዋል። ይህ ለማንኛውም ኢንቨስተር በህንድ በአምራች አገልግሎት ለመሳተፍ ለሚፈልግ ትልቅ እድል በመፍጠር ለክልል ገበያዎች አቅርቦት መሰረት ይሆናል። ተመሳሳይ ሁኔታ የጥገና እድሳት እና ኦፕሬሽን አገልግሎቶች ማቋቋም ጋር በተያያዘ ግልጽ ነው። ለአቬሽን እቅድ መሳካት በህንድ የአቬሽን ዘርፍ ኢንቨስት ለማድረግ ትክክለኛ ጊዜ አሁን ነው።

ህንድ በመከላከያ እና ህዋ ላይ ኢንቨስት እንድታደርጉ ትጋብዛለች። “የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት” ገደብም ለኢንቨስትመንት በመከላከያ ዘርፍ ወደ 74% ከፍ አድርገናል። ህንድ የመከላኬ መሳሪያዎችን እና እቅዶችን ምርት ለማበረታታት ሁለት የመከላከያ ኮሪደሮችን አቋቁማለች። ለግሉ እና ለውጭ ኢንቨስተሮች ልዩ ማበረታቻ እናቀርባለን። ከጥቂት ሳምንታት በፊት በህዋ ዘርፍ ላይ ወሳኝ ለውጥ አካሄደናል። ኑ እና የእነዚህ ዘርፎች ተጠቃሚ ይሁኑ።

ህንድ በፋይናንስ እና በኢንሹራንስ ኢንቨስት እንድታደርጉ ትጋብዛለች። ህንድ “የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት” ገደብን  በኢንሹራንስ ላይ ወደ 49% አሳድጋለች። በአሁኑ ሰዓት መቶ በመቶ “የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት” ለኢንሹራንስ እና ለአገናኞች ተፈቅዷል። የኢንሹራንስ ገበያ በህንድ ከ12% በላይ እድገት ምጣኔ ያለው ሲሆን እ.ኤ.አ በ2025 ወደ 250 ቢሊየን ዶላር እንደሚያድግ ይጠበቃል። በአዩሽማን ባራት ስኬት መሰረት የጤና ኢንሹራንስ እቅዳችን ተሳክቷል፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ፋሳል ቢማ ዮና የእኛ የሰብል ኢንሹራንስ እቅድ እና ጃን ሱራክሻ ወይም የማህበራዊ ዋስትና እቅድ መንግስት የኢንሹራንስ ምርቶችን በፍጥነት ለመስጠት እና ተቀባይ ለማድረግ መንገዱን አመቻችቷል። በጤናው ዘርፍ፣ እርሻ፣ ንግድ እና የህይወት ኢንሹራንስ ሽፋን ትልቅ ጥቅም ላይ ያልዋለ የኢንሹራንስ ሽፋን እድል አለ። የረጅም ጊዜ ገቢን ለማረጋገጥ የህንድ የኢንሹራንስ ዘርፍ በአሁኑ ሰዓት አንዱ እና ተመራጭ ኢንቨስትመንት ነው።

ጥቂት አማራጮች ያለ ማማከር ክፍያ ሰጥቻችኋለሁ።

**ክቡራን ወዳጆች**

ገበያዎች ሲከፈቱ እድሎች ከፍተኛ ሲሆኑ እና አማራጮች በርካታ ሲሆኑ ከፍተኛ አዎንታዊ አማራጭ ይገኛል። ህንድ በንግድ ደረጃ ያላትን ከፍተኛ እድገት መመልከት ይቻላል። በተለይም በአለም ባንክ በቀላሉ ስራ የሚሰራበት የተሰጣት ደረጃ መመልከት ይቻላል።

ኢንቨስትመንት የበለጠ በራስ መተማመን ያሳያል። በየአመቱ “የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት” ከፍተኛ ሪፖርት እያስመዘገብን እንገኛለን። በየአመቱ ካለፈው አመት የበለጠ ውጤት እያስመዘገበ ነው። በህንድ የኤፍዲአይ ፍሰት በ2019-20 ሰባ አራት ቢሊየን ዶላር ነው። ይህ ጭማሪ ካለፈው አመት በፊት ከነበረው 20% ጨምሯል። በዩኤስአይቢሲ ያሉ ወዳጆቻችን የኢንቨስትመንት ፍሰት ከዩናይትድ ስቴትስ በዚህ አመት ከ40 ቢሊየን ዶላር በላይ መሆኑን ገልፀውልናል።

ከዚህ በተጨማሪ አሁን ባለው ወረርሽኙን የተከሰተውን መመልከት ይቻላል። በኮቪድ ወረርሽኝ ወቅት ከሚያዝያ እስከ እ.ኤ.አ ሐምሌ 2020 ህንድ ከ20 ቢሊየን ዶላር በላይ የውጭ ኢንቨስትመንት ስባለች።

ነገር ግን ህንድ የበለጠ እድሎች አቅርባለች። የአለም አቀፍ ኢኮኖሚ እንዲያገግምየሚያስፈልገውን እናደርጋለን።

**ክቡራን ወዳጆች**

የህንድ ማደግ ማለት በንግድ አማራጮች በአለም አቀፍ ኢኮኖሚው ላይ እምነት የሚጣልባት ሀገር መሆኗን ያሳያል። በኢንቨስትመንቱ ላይ የሰለጠነ የሰው ሀብት በመኖሩ ያተርፋል።

**ክቡራን ወዳጆች**

ለዚህ ራዕይ ከዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ የተሻለ አጋር ብዙም የለም። ህንድ እና ዩኤስኤ የጋራ እሴቶች ያላቸው ዲሞክራሲ ያበበባቸው ሀገራት ናቸው። እኛ የተፈጥሮ አጋሮች ነን። የዩኤስ-ህንድ ወዳጅነት ባለፉት አመታት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። አሁን የእኛ አጋርነት አለም ከወረርሽኙ በኋላ በፍጥነት እንዲያገግም ለመርዳት ጠቃሚ ሚና ይጫወታል። የአሜሪካ ኢንቨስተሮች ወደ ዘርፉ ወይም ወደ ሀገሪቱ ለመግባት ትክክለኛውን ጊዜ እየተጠባበቁ ይገኛሉ። ለእነርሱ በህንድ ኢንቨስት ለማድረግ ከአሁኑ የተሻለ ጊዜ እንደሌለ ለመናገር እፈልጋለሁ።

ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ የዩኤስአይቢሲ አመራር የህንድ-ዩኤስ የኢኮኖሚ አጋርነቱ ለማጠናከር ስላላቸው ቁርጠኝነት ለማመስገን እወዳለሁ።

የህንድ-አሜሪካ አጋርነት የበለጠ ይደግ!
ሰላምታ
አመሰግናለሁ
ኒው ደልሂ

ሐምሌ 15/2012 ዓ.ም